# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org

ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ

Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band


***የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ***
***ህዳር 3 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ***

## ነፃ ተቋማት

እንደ ማንኛውም ሀገር ኅብረተሰብ ሁሉ ፣ ሀገራችንም በተዋረድ፣ ከቤተሰብ ጀምሮ እስከ መንግሥት ድረስ በተካተቱ ተቋማት ማዕቀፍ ውስጥ የኖረች ሀገር ነበረች። ነባሮቹ ተቋማት፣ የታሪክ፣ የዕምነትና የባኅል ዕሴቶችን መሠረት አድርገው ለሀገሪቱ ኅልውና ለሕዝቧም አብሮ መኖር መሠረት ሆነው ቆይተዋል። በማኅበራዊ ኑሮ መስክ ፣ ነገሥታቱ በፖለቲካው ፣ መሬት ደግሞ በኢኮኖሚውና በአንኗኗሩ ዘንድ የየራሳቸው ድርሻ ነበራቸው ለማለት ነው ። መሬት ወሳኝና ስትራተጂያዊ ሀብት በመሆኑ የሀገሪቱ ዘለዓለማዊ ተቋም ሆኖ መቆየቱ አከራካሪ አይደለም ።

ሁሉም እንደ ተቋማት ፣ በፖለቲካውና በኢኮኖሚው መስክ በሕዝቡ ላይ የነበራቸው ተጽዕኖ የተለያየ ቢሆኑም፤ በተናጠልም ይሁን በጋራ፣ ለሀገሪቱ በነጻነት መቆየት የየድርሻቸውን አበርክተዋል ቢባል ስህተት አይሆንም ። የመሣፍንቱ መሪር አገዛዝና የመሬት ጉልተኞች ሥርዓት ዝርፊያና ብዝበዛ፣ መጠን-የለሽ የነበረ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፣ ዜጎቿም እንደ ሕዝብ አብረው እንዳይኖሩ ግን አላደረጉም ። ይህንን ሃቅ ለመቀበል የሚከብዳቸው፣ ተገንጣይና አስገንጣይ ቡድኖች ብቻ ናቸው ።

ነባር ተቋማቱ ባኅላዊ፣ ሃያማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ስለነበሩ፣፤ ሁሉም እንደ አግባብነታቸው በየፈርጁ ሲያደርጉት የነበረው የአሰራር ድርሻ በሕዝቡ ላይ ያሳረፈው አንደምታ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም ። ከሃይማኖት መርሀ-ግብር አኳያ " **የመለኮትን ለመለኮት ፣ የቄሣርንም ለቄሣር** " የሚል አስተምህሮ ቢኖርም፤ ሁሉንም አጠቃልሎ በመያዝ የአራጊ -ፈጣሪ ሥልጣን የያዘው የነገሥታቱ አገዛዝ እንደ ነበረ አሌ የሚባል አይደለም ። በዚህ ምክንያት፣ የተቋማቱ ነጻነት ታፍኖና ጫጭቶ የኖረ ነበር ቢባል እንደ ማጋነን አይቆጠርም ። የሰው ልጅ፤ በግልም ሆነ በወል ፣ ራሱን ነጻ ካላደረገ በስተቀር፤ ነጻ ተቋማትንም ሆኑ ፣ ነጻ ህይወቱን ሊመራ አይቻለውም። ታዲያ፣ የራስንም ነጻነት ከማግኘትና ከማረጋገጥ የበለጠ ደግሞ ሀብት ሊኖረውም ከቶ አይችልም ።

የሀገራችን ኋላ ቀር ኢኮኖሚ ደረጃና የፖለቲካ ሥርዓቱም እጅግ ሲበዛ በአምባገነን አገዛዝ ስር በመሆኑ ምክንያት ፣ ነጻ ተቋማት ደብዛቸው የጠፋ ሆኖ ይኖራል ። የዴሞክራሲ ጭላንጭል በማይታይበት ሀገር ፣ ይህ መሆኑ ባያስገርምም፣ የሕዝብ ነጻነት ሳይረጋገጥ፣ ነጻ ተቋማት ይኖራሉ ብሎ ማሰብ እንኳን የህልም እንጀራ ነው ። የጥንት ገዥዎች፣ ለሥልጣናቸው ማጠነከሪያ፣ ለህይወታቸውና ለዕድሜያቸው ማራዘሚያ ፣ ባኅላዊ ዕምነትንና የሃይማኖት ተቋማትን በመሳሪያነት እንደ ተጠቀሙባቸው ሁሉ፤ የዘመኑ መንግሥታት ነን የሚሉት ገዥዎች ደግሞ፤ አምባገነን ሥርዓታቸውን ለማስፈንና ሥልጣናቸውን ለማደላደል ሲሉ፣ ሁሉንም ተቋማት በመዳፋቸው ስር አስገብተው ለመጨቆኛ መሳሪያ ይገለገሉባቸዋል።

የቆዩቱ  መንግሥታት፣  ሃይማኖትን ፣ የፖለቲካ መሳሪያ አድርገው  እየተጠቀሙ፣ የሚገዙት ሕዝብ እንዲያመልክባቸው ያደርጉ እንደ ነበር የቅርብ ትዝታ ነው ። የወቅቱ ገዥዎችም፣ የሃይማኖት ተቋማትን ነጻነት በመገፈፍ፤ ለፖለቲካቸው ተዋናዮች እያደረጓቸው ይታያሉ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ  ቤተክርስቲያን፤  ነጻ የሃማኖት ተቋም መሆኗ ቀርቶ፣  በዘር  ላይ ለተመሰረተው  የወያኔ  ፖለቲካ ማስፈጽሚያ መሳሪያ እየሆነች ነው ።  የሃይማኖት መሪዎችም የፖለቲካ አራማጆች መሳሪያ መሆናቸው፤ ምዕመናኑን እያሳዘነው ይገኛል። በአሁኑ ጊዜ፣ ነፃ የሃይማኖት ተቋማት  ደብዛቸው ጠፍቷል ።

የጥንት ገዳማትና መካነ አምልኮትም በበኩላቸው፤ ነጻ ተቋማት  መሆናቸው እየቀረ፤ እንዲያውም ከነአካቴው ኅልውናቸው እንዲጠፋ እየተደረገ ነው ።  በወያኔ  ዕምነት፣ ነጻና ጥንታዊ  ተቋማትን ማጥፋት ማለት፣ የኢትዮጵያ  ጥንት- መሠረት  የሆኑትንና የሀገሪቱን  ማንነት ገላጮች ሁሉ ለምስክርነት እንዳይቀዩ ከምድረ- ኢትዮጵያ   ማስወገድ  ማለት  ነው።  ይህ የሚሳካለት ከሆነ  ደግሞ፣ ወያኔ - ሰራሽ  ሀገር ለመፍጠር  ይመቸዋል ።  ይህ ሁኔታ አይከሰትም ብሎ  መዘናጋት፣ ከየዋህም የዋህነት ነው ። ዔርትራን ያስገነጠለ ቡድን፣  የኢትዮጵያን  ህልውን ደብዛ ከማጥፋት  ይቆጠባል  ተብሎ  አይታሰብም ። ይህንንም ሃቅ በይበልጥ ለመረዳት፣ የወያኔ አመራር አባል የነበረው ግለሰብ  ስሞኑን  ያወጣውን  መጽሐፍ ማገላበጡ  አይከፋም ።  " **ከባለቤቱ  በላይ  ያወቀ  ቡዳ**  "  ነውና !

የሀገራችን  የእስልምና ሃይማኖት እንደዚሁ፣ በነጻነቷ ተከብራ ምዕመናኗን  ለማገልገል የሚያስችላትን ነጻነት ስለተገፈፈች፣  ነጻ ሃይማኖታዊ ተቋምነቷን  አጥታለች ።  ዛሬ  የኢትዮጵያ  ሙስሊም  ዜጎቻችን ፣ እንደ ሌሎቹ   ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፣ የግል   ነጻናታቸው  መገፈፉ  ብቻ  ሳይሆን፣  የሃይማኖት ተቋማቸውም  ጭምር  ነጻነታቸውን  አጥተዋል ። የሀገራችን ተቋማት  ሙሉ  ነጻነት የማግኘት  ጉዳይ ከመሠርታዊው የዴሞክራሲ መብትና ነጻነት ጋር የተቆራኘ  ስለሆነ፣  በኢትዮጵያ  የዴሞክራሲ  ሥርዓት እስካልተረጋገጠ  ድረስ፣  ማንኛውም ተቋማት ነጻ ሊሆኑ አይችሉም  ።

ማንኛውም መንግሥት ነጻ መንግሥት  ሊሆን የሚችለው፣ የሀገሩን ሉአላዊነትና እመራዋለሁ የሚለውን ሕዝብ ነጻነት እስካከበረ ደረስ ብቻ ነው ። የሌሎቹን ነጻነት የነፈገ፣ የራሱን ነጻነት  ያገኛል  ማለት  ዘበት ይሆናል ።  ማነኛውንም ድርጅት ሆነ ተቋም፣  ነጻነት ለማግኘትና ለማረጋገጥ  ከፈለገ፤ መጀመሪያ  የራሱን ነጻነት ማረጋገጥ  ወሳኝ መሆኑን ማወቅ ይገባዋል።   ነጻ ተቋማት እንዲኖረው የሚመኝ  ሰው፤  ከሁሉ አስቅድሞ፤ የራሱን  ጭንቅላት ለማንም አለማስገዛቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል ። የራስን ጭንቅላት/ ኅሊና አለማስገዛት ማለት፣ የራስን ነጻነት እንደ  ማስከበር ይቆጠራል ማለት ነው ።  የግል ነጻነትን አስድፍሮና በሰብዕናውም ላይ  ከተደራደረ  በኋላ ፣ ስለ ነጻ ሀገርና ነጻ  ተቋማት ለማሰብ  ኅሊና አይኖረውም ። ከማንኛውም ነጻነት ማጥት የከፋው፣ የኅሊና ነጻነትን አለማግኘት ነው ።  በደመ- ነፍስ ብቻ የሚንቀሳቀስ ሰው፣  ለመኖር ብቻ ሲል የሚኖር ፍጡር ከመሆን አያልፍም ።

አምባገነን  ገዥዎች ይህንን  ደህና አድረገው ስለሚያውቁ፣  የሚገዙትን ሕዝብ ኅሊና በኀይል እያስጨነቁ፣ እያንኮታኮቱና እያዳሸቁ ኅሊና ቢስ እንዲሆን ማድረግ ነው።  ኅሊና- ቢስ ከሆነላቸው በኋላ፣ እንዳሻቸው ለመግዛት  ያመቻቸዋል ።  ነጻና የነቃ ኅሊና ያለው ሕዝብ  ማንም  እንዲገዛው  አይፈቅድም  ።  ነጻ

ተቋማትን እያከበረና እየጠበቀ ነጻነቱን አስከብሮ በነጻነት ይኖራል እንጅ ! ይህንን ማድረግ ደግሞ ፤ በታሪካቸው ለኢትዮጵያን አዲስ አልነበረም ። የአሁኑ ግን ሌላ ጉዳይ ነው።

የማንኛውም ሀገር ሕዝብ ነጻ ሀገር አለኝ ብሎ መተማመን የሚችለው፣ የዴሞክራሲ ዋና ምሶሶ የሆኑት ሦስት መሠረታዊ ነፃ ተቋማት ሲኖሩት ነው ። እነርሱም፣ ነጻ ፕሬስ፣ ነጻ ዳኝነትና ነፃ ተቃዋሚ ናቸው ። እነኝህ ነፃ ተቋማት፣ የሕዝቡን ነፃነት ለማረጋገጥ፣ አንድም ሦስትም ናቸው ። ስለሆኑም የሕዝቡ የነቃ ትብብርና ድጋፍ ሊነፈጋቸው አይገባም ። በሕዝብ ምርጫና ፈቃድ የማይመጣ መንግሥት ሁሉ፣ የተደራጀ ጭራቅ ነውና ማንም ሊያምነውና ሊቀርበው አይችልም ። የራሱ እንጅ፣ የሕዝብ ያልሆኑ ተቋማትን አደራጅቶ የማፍያ ተግባሩን የሚያከናውንበትን ዕርምጃ ይቀጥላል ። እነኝህ ተቋማትም፡-

- የጦር ኃይል፣
- የደኅንነትና የፖሊስ ድርጅት፣
- የገንዘብ ምንጭ ፣
- የፕሮፓጋንዳ መ/ ቤትና
- የውጭ ግኑኝነት ( ዲፕሎማሲ ) ናቸው።

እንደ መንግሥት፣ የሕዝብ መሠረት ስለማይኖረው፣ ከላይ የተዘረዘሩትን ተቋማት መቆጣጠሩ ብቻ ዘላቂ ማስተማመኛ ሊሆነው አይችልም ። የሕዝብ ተዓማኒነትም ሆነ አክብሮት ስለሌለው ፤ አንድነቱና ውኅደቱ እውነተኛ አይደለም ። እየቆየ በሄደ ቁጥርም ፤ ውስጡ እየተቦረቦረና በተለያዩ ቡድኖች ( ፋክሽንስ ) መከፋፈሉ ስለማይቀር፤ እርስ በእርሱ መበላላቱ ይቀጥላል ። ይህ የሚሆነው፣ ቢጋራ የዘረፉትን የሕዝብ ሀብት መከፋፈል በሚፈጥሩት ትርምስ ነው ። በአሁኑ ወቅት፤ በቅሌትና በሙስና፤ በጉቦና በዝርፊያ እርስ በእርሱ የሚካሰሰው፤ የሚበላላውና ገሚሱ እየኮበለለ ቀሪው ደግሞ ወደ እስር ቤት የሚወረወርው የወያኔ መንጋ እንደ ምሳሌ ይወሰዳል ። ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ በሻዕቢያና በወያኔ መካከል የተካሄደው ጦርነት፣መንሰዔው፣ የኢትዮጵያን ሀገራዊ አንድነት ለማስጠበቅ ሳይሆን፣ የሀገራችንን ሀብት ለመዘረፍ በመካከላቸው የነበረው የሽርክና ገመድ በመበጠሱ ነበር።

ሙስናም ሆነ የሥነ ምግባር ብልሹነት፤ ብክለትና ከእነኝህ ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ መጥፎ ባኅርያትና ድርጊቶች ሁሉ መነሻቸው፤ አንዱና ዋነኛው የነጻ ተቋማት አለመኖር ነው ። ነፃ ተቋማት ደግሞ የዴሞክራሲ ሥርዓት ካልሰፈነ ሊመጡ አይችሉም ። ይህ በሆነበት ሀገር የሕዝብን ችግር ማሰወገድ ቀርቶ፤ ችግር መኖሩን እንኳን ማየት ይቸግራል ። ችግሩ ታይቷል ቢባልም እንኳ፤ ችግሩ የሚታይበት አቅጣጫ የተሳሳተ ከሆነ፤ መፍተሄ ለማግኘት ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። ራሳቸውን ነፃ ያላደረጉና የሕዝብ ዕምነት የተነፈጋቸው መሪዎች

ደግሞ፤ ችግሮችን ለመፍታት ቁርጠኞች አይሆኑም። ምክንያቱም የታመቀውን ችግር ለመፍታት የሞከሩ እንደሆነ የአጋንንት በረት ይከፈትባቸውና የሚይዙት የሚጨብጡትን ያጣሉ። ከዚህ የሚቀጥለው ያ ፈለጭ -ቆራጭ የነበረው ሥርዓት እንደ እንቧይ ካብ እየተናደ መፈረካከስ ይሆናል ።

" **መልከ - ጥፉን በስም ይክሱ** " እንዲሉ፤ ወያኔ፤ ዘረኛ ሥርዓቱን ያወደሰ እየመሰለው ፤ የስም መለዋወጥ ቁማር ይጫውታል ። አብዮታዊ ዴሞክራሲ ፤ ልማታዊ መንግሥት፤ ኢሕአዴግ መራሹ ፤ ወዘተ. እያለ ራሱን ይደልላል ፡፡ የወያኔ ዴሞክራሲ ፤ ልክ አላዋቂ እንደሰፋው ተነፋነፍ ሱሪ ከባቱ ላይ የጠበበ በመሆኑ፤ እግርን ጠርንፎ በመያዝ የማያፈናፍን ይሆንና ከጉልበት በላይ ያለው ቅርፅ ግን ሰፊና ተነፋነፍ ይሆናል ። ሰፊው ዴሞክራሲ ለወያኔና ለኣባላቱ ይታደላል ። መላው ሕዝብ ግን መፈናፈኛ በሌለው ማንቆ ተጠፍንጎ ተይዟል።

የወያኔ አብዮታዊ ዴሞክራሲና ስብዓዊ መብቶች የሚሰጡት ለወዳጅ እንጂ ለጠላት የሚተርፉ አይደሉም። የወያኔ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ፤ ዜጎችን ፤ ወዳጅና ጠላት ብሎ በመፈረጅ የሚከፋፍል ከይሲ ሥርዓት እንጅ፤ የዴሞክራሲ ቃናም ይሁን ንክኪት የለውም ። ተባባሪያችን ሊሆን አይችልም ብለው የሚጠረጥሩትን ለማጥቃትና ለማጥፋት ይጠቅሙበታል ። ይህ ነው እንግዲህ፤ የወያኔ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለው ጉድ። ልማታዊ መንግሥት ነኝ የሚለው ደግሞ፤ ሌላው አስቂኝ ጨዋታው ነው ። ልማት የሚባለው፤ ለራሱና ለወገኖቹ እንጅ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቤሳ ቤስቲን አይተርፈውም ። ኢሕአዴግ መራሹ የሚባለው ዳንኪራ ደግሞ፤ ወያኔ ከነከበሮው ወደ የማይቀርለት ጉድጓድ የሚወረወርበት የማብቂያው ሂደት ይሆናል ።

ወያኔ፤ የአንድን የገዥ ፓርቲ የበላይነትና በስሩ ያለውን የመከላከያ ሃይል ተጠቅሞ፤ የሁሉንም መንግሥታዊ ተቋማት መቆጣጥሩን አረጋግጧል ። የምክር ቤቱን፣ ሥራ አስፈፃሚውን፣ ፍትኅንና ፀጥታን በመዳፉ ውስጥ አስገብቶ ያሻውን ለማድረግ ችሏል ። ይህ ሁኔታ ደግሞ፤ የመደብለ- ፓርቲ ዕድገትን ከማቀጨጨም በላይ፤ ነፃ ተቋማት እንዳይፋፉና እንዳይስፋፉ አድርጓቸዋል ። በፍርሃት፤ በጭንቀትና በስጋት የተሸበበ ሥርዓት በመሆኑ፤ በራሱ በወያኔ ውስጥ የሚነሱትን ጥያቄዎች እንኳን ሳይቀር ለማስተናገድ ድፍረት አይኖረውም። በመሆኑም መፍተሄ-አልባ ችግሮችን ታቅፎ ፤ ግበዓተ መሬቱን ይጠብቃል ። መርኅ-አልባ የሆነ ድርጅት ፤ ራዕይና አቅጣጫ ስለማይኖረው፤ በጭፍን ለመጓዝ ይገደዳል ። ሀገራችን ኢትዮጵያም ባለቤት ያጣች ሀገር ሆናለች ።

ይህች ባለቤት ያጣች ሀገር፤ ሙያዊ ብቃትና በሥነ ምግባር የታንፁ መሪዎች ከሌሏት፤ የሁሉም መሆኗ ቀርቶ፤ የማንም ሳትሆን ትቀራለች ብለው የሚሰጉ አያሌ የፖለቲካ ተንታኞች አሉ ። በእኛ ዕምነት፤ የትምክህትና የጠባብ ብሄረተኛ ፖለቲካ መነሻ ፤ በሥልጣን ለመቆየት የሚጠቀምቡት የአምባገነኖች ስልት ነው ። የወያኔ ቅይጥ- መርህ እስካሁን ድረስ ጥፋትን እንጅ፤ በጎ ጉዳይን አላስመዘገበም ። በአሁኑ ወቅት፤ ወያኔ ራሱ

እንደ ድርጅት መስራት እየተሳነው፤ የተወሰኑ ግልሰቦች ኀይላቸውን አሰባስበውና አጠናክረው፤ ደኅንነታቸውንና ኀልውናቸውን መጠበቂያና ማቆያ አድርገውታል። ታዲያ ይህ ከሆነ ፤ ከሕዝቡና ከተቃዋሚው ጎራ ምን ይጠበቃል?

- ትግሉን አቅጣጭ ለማሲያዝ፤ ፍኖተ- ካርታ ( ሮድ ማፕ) መቅረፅ አስፈላጊ ነው ።
- የስበት ማዕከሉን ( ሴንተር ኦፍ ግራቪት ) መቀየርና መቆጣጠር ወሳኝነት ይኖረዋል ።
- የፖለቲካ ትኩሳቱን ማቀጣጠልና ማራግብ ፤ የወያኔን ዕድሜ ያሳጥረዋል ።
- ወያኔ፤ ወደ ክፍተኛ ውጥረት እየገባ ያለ አገዛዝ በመሆኑ፤ በተረጋጋና በሰከነ አዕምሮ የሚያስብበት ክኅሎት ያጣ መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው ።
- ኢትዮጵያ ፤ በታሪኳ፤ ዛሬ ፤ ባለቤት ያጣች ሀገር መሆኗን ተረድቶ ፤ ዜጎቿን መታደግ የሁሉም ድርጅትና ታጋይ የቅድሚያ -ቅድሚያ አጀንዳ መሆኑን ማመን ያስፈልጋል ።
- ሀገራዊ ጥሪውን መቀበል፤ ማስተለለፍ፤ መስማትና መተባበር የሁሉም ዜጋ ኀላፊነት በመሆኑ፤ እኛም በበኩላችን ፤ ጥሪውን አናስተላለፋልን፤ እንቀበላለን፤ እንተበበራለን !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !!!